# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

14



ኅዳር ፲፰ —፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንዲሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።

# የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር

## ፲ኛ ትምህርት ከን - ዓ

ኅብረተሰብ በመደቦች ከተከፋፈለበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬ ድረስ ብዙ ሰዎች ግፍ ፤ በደል ብዝበዛና ጦርነት ሁሉ የሚቀርበት ሰዎች በወንድማማችነት ፤ በሰላምና በእኩልነት ብልጽግና የተሞላበት ኑሮ የሚኖሩበት ኅብረተሰብ በመሻት አልመዋል ፤ ጽፈዋል ፤ ተፈላስፈዋል ፤ ታግለዋል ተሰውተዋል ። ነገር ግን ማርክስና ኤንግልስ ባለፈው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ጠቅላላውን የዓለም ታሪክ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አጥንተው ይህ ብዝበዛና በደል የሌለበት ፤ መደቦችና የመደቦች ትግል የሌለበት የእኩልነትና የብልጽግና ዘመን ወደፊት የማይቀር ነገር መሆኑን ብቻ ሳይሆን በእንዴት ዓይነት ትግል ሊመጣ እንደሚቻል መንገዱን እስኪያሳዩ ድረስ ይህ የሰዎች ቅንምኞት ሕልም እንጂ ተጨባጭነት አልነበረውም ።

ማርክስና ኤንግልስ ወደፊት መደብ የለሽ ኅብረተሰብ ይመጣል ብለው በቁርጠኝነት የተናገሩት ሕልመኞች ሆነው ሳይሆን ያለፈውን የኅብረተሰብ አስተዳደግ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተንተነው የኅብረተሰብ አስተዳደግ እንደማንኛውም ነገር የዲያሌክቲክስን የለውጥ ሕግጋት እንደሚከተል ተመልክተውና የምርት ኃይሎች በምንም ዓይነት የማያቋርጥ እድገትና ምርት የማያቋርጥ መደብር ለተትረፈረፈና መደብ የለሽ ለሆነ ኅብረተሰብ ጽኑ የኢኮኖሚ መሠረት እንደሚሰጥ በማያሻማ ሁኔታ በማወቃቸው ነው ።

በኮሚኒስት ኅብረተሰብ ብዝበዛና ጭቆና የሚባል ነገር ጨርሶ የለም ። ግን ደግሞ ይኸ ብቻ አይደለም ፤ የኮሚኒስት ኅብረተሰብ የምርት ኃይሎች ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ደረጃ የደረሱበት ኅብረተሰብ ነው ። በዚህ የተነሳ የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ምርትም እንደዚሁ በከፍተኛ ደረጃ ይገኛል ። ስለሆነም ይህ ሥርዓተ ማኅበር የተትረፈረፈ ሥርዓተማኅበር ነው ። በጥንቱ የጋርዮሽ ዘመን ብዝበዛ የሚሉነገር ፤ መደብ የሚሉ ነገር ያልነበረው ምርት እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለነበረ የሆነውን ያህልመጭው የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ደግሞ ብዝበዛ አልባና መደብ አልባ የሚሆነው ምርት እጅግ ስለሚትረፈረፍ ይሆናል ። ኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ማንም ሰው የሚያስፈልገውን ነገር በሚያስፈልገው መጠን የሚያገኝበት የበለጸገ ሥርዐተ ማኅበር ነው ። ስለሆነም የሥርዓተ ማኅበሩ መፈክር «ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ፤ ለእያንዳንዱ እንደፍላጎቱ» ይሆናል ።

የኮሚኒስት ሥርዓተ ማኅበር ሕልም አይደለም ። በምርት ኃይሎች ማደግ ፤ በምርት ግንኙነቶች በአብዮታዊ መንገድ መቀየርና በምርት መትረፍረፍ ላይ የሚመረኮዝ ሥርዓተ ማኅበር ነው ። እንደዚህም በተጨባጭ ሁኔታ ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚመጣ ኅብረተሰብ ስለሆነ በአንድ ቀንሌሊት አይደረስበትም ። ምርት ካልዳበረ ደግሞ ምን ያህል ብንመኘው አናገኘውም ። ስለሆነም ካፒታሊስት ኅብረተሰብ በፈራረሰ በማግሥቱ ኮሙኒስት ኅብረተሰብ አይደረስበትም ። ለተትረፈረፈው የኮሙኒስት ኅብረተሰብ ዝግጅት የሚደረግበት የሽግግር ዘመን ያስፈልገዋል ። ይህ የሽግግር ዘመን የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ወይም ዝቅተኛው የኮሙኒስት ሥርዓተ ማኅበር ነው ። ሌኒን እንዳለው ።

«ከካፒታሊዝም የሰው ዘር ሊሸጋገር የሚችለው ወደ ሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ብቻ ነው። ይህም ማለት የምርት መሣሪያዎችን በጋራ ሀብትነት ይዞ በክፍያም በኩል ለእያንዳንዱ ግለሰብ ባበረከተው ሥራ ልክ የሚካፈልበት ኅብረተሰብ ነው ማለት ነው ። የኛ ፓርቲ ግን ከዚህ ባሻገርም

ይመለከታል ። ሶሻሊዝም ቀስ በቀስና የግድ ወደ ኮሙኒዝም መለወጥ አለበት ። »

የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር እንዳለፉት ሥር ዓተ ማኅበራት ብዝበዛን አያውቅም ። እንደመ ጭው የኮሙኒስት ሥርዓተ ማኅበር ደግሞ ገና የተ ትረፈረፈ ስላልሆነ ለእያንዳንዱ ግለሰብ የፈለገ ውን ሁሉ በፈለገው መጠን ሊሰጠው አይችልም።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከዕለት ዕለት እየተራቀቁና እያደጉ የሚሔዱት የምርት መሣ ሪያዎች በሙሉ የሠራተኛው ሕዝብ የጋራ እንጂ የጥቂት ግለሰቦች ሀብት አይደሉም ። ስለሆነም በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጉልበት እየበዘበዘ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ የወዝ ፍሬ እየተንደላቀቀ የሚኖር መደብ ወይም የኅብረተሰብ ክፍል የለም ። ሁሉም የሥራውን ፍሬ ያገኛል ። የማይሠራ ደግሞ አይበላም ። ማንም የሥራው ፍሬ አይነፈገውም ግን ደግሞ ሁሉም እኩል አይከፈልም ። በዚህ በኩል የሥር ዓተ ማኅበሩ መፈክር ከኮሙኒስት ሥርዓተ ማኅበር የተለየ ነው ። «ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእ ያንዳንዱ እንደሥራው» የሚል መፈክር ነው ።

ከካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ወደኮሙኒ ስት ሥርዓተ ማኅበር በሚደረገው የሽግግር ዘመን «ያኛው ወደዚህኛው የሚለዋወጥበት የፖለቲካ ሽግግር ዘመን አለ ። ይህም የወዝ አደሩ አብዮ ታዊ አንባገነንነት የሰፈነበት መንግሥት ከመሆን ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም » ይላል ማርክስ ።

በወዝአደሩ አንባገነንነት ሥር የሚካሄደው የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ኢኮኖሚው በዘፈቀደ የሚ ሠራ ኢኮኖሚ ሳይሆን አቅጣጫና አጢቃላይ ፕላን የሚከተል ኢኮኖሚ ነው ። በዚህ ኅብረተሰብ ምርት ለግለሰብ ለትርፍ ሳይሆን የጠቅላላውን ሠራተኛ ሕዝብ ኑሮ ከዕለት ዕለት ለማሻሻልና ወደ መደብ አልባው ሥርዓተ ማኅበር ለሚደረገው ሽግግር አስፈላጊውን የማቴሪያል ዝግጅት ለማድ ረግ ነው ። የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር በፕላን የሚመራ በመሆኑ በሳይንስ ፤ በቴክኖሎጂ በኅብ ረተሰቡ የተፈጥሮና ሰብአዊ ሀብት በሚገባና መዝ ረክረክን በማያውቅ ዘዴ ይጠቀማል ።

በወዝ አደሩ መሪነት ካፒታሊዝምን ደምስ ሰው ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ ያሉ አገሮች ብዙ ናቸው ። እነዚህ አገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ድንቁርናን ፤ ድህነትን ፤ ብዝበዛን ከሀገራቸው ገጽ አስወግደዋል ። ትምህርት ብቻ ሳይሆን ነፃ የሕክምና አገልግሎት ስለሚሰጡ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ጤንነት ዘመናዊ ሳይንስ በፈጠራቸው ጥበ ቦች ሁሉ ይንከባከባል ። ሥራ አጥነት ጨርሶ የለም ። ሴተኛ አዳሪነት የለም ። የኅብረተሰቡ ግማሽ የሆኑት የሴቶች የብዝበዛና የድርብ ጭቆና ምንጭ የነበረው የግል ሀብት የወደመውን ያህል ሠርቶ አዳሪ ሴቶች ከወንድ ተጽእኖ ተላቀው በእ ኩልነት ይኖራሉ ።

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ለኮሚኒስት ሥር ዓተ ማኅበር አስፈላጊ የሆነው የመትረፍረፍ የምርት ደረጃ ገና በየትም አልተደረሰበትም ። ከላይ እንዳልነው ኅብረተሰቡ «ከእያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ» በሚለው መፈክር ስር መሰለፍ የሚቻለው አስቀድሞ በወዝ አደሩ አንባገነንነት እየተመራ የምርት ኃይሎችን ከፍተኛ ደረጃ አድርሶ በሀብት ሲትረፈረፍ ብቻ ነው ።

## የሶሻል ዲሞክራሲ . . .

ከ፳፯ኛው ገጽ የዞረ

ብቅ እንደማይችል አስቀድመን አይተናል ። አሁን ደግሞ ከሌላ አቅጣጫ እንየው ። የማርክሲዝም ሌኒ ንዝም ሀ.ሁ. እንደሚያስተምረን ወዝአደሩ ያለፓ ርቲው ሥልጣን ሊይዝም ሆነ በሥልጣን ሊካ ፈል አይችልም ።

«ወዝአደሩ በዚህ (በዲሞክራሲያዊ) አብዮት የመሪነቱን ሚና ሊይዝ የሚችለው ትግሉን በርእ ዮተዓለምና በገቢር በሚመራ ዲሞክራሲያዊ (በወ ዝአደሩ) ፓርቲ ጥላ ሥር እንደ አንድና ነፃ የፖ ለቲካ ኃይል ሲዋሐድ ብቻ ነው ። » (ሌኒን ገጽ ፳፫ ስርዝና ቅንፍ የተጨመረ)



ወዝአደሩ ያለፓርቲው ባለበት ጊዜ ይህን ጥያቄ በእሱ ስም ማቅረብ በወዝአደሩ ስም መነ ገድ እንደሆነ ግልጽ ነው። ገበሬውስ ? ገበሬው ደግሞ ከኢኮኖሚ አቋሙ የተነሣ ባጠቃላይ ሲታይ በቡር ዥዋውና በወዝአደሩ መሀከል እንደሚዋልል ሌኒን አሳይቷል ። ማርክስ እንዳረጋገጠውም ገበሬው «በራሱ ስም የራሱን መደብ ጥቅም ሊገፋበት » ስለማይችል ወይ በቡርዥዋው ፤ በንዑስ ከበርቴው አለበለዚያም በወዝአደሩ አማካይነት ካልሆነ ራሱን በቀጥታ ወክሎ በሥልጣን ሊሳተፍ አይችልም ።

ቡርዧዋው አብዮቱን ከከዳ ወዲህ ገበሬው ለመሬትና ለነፃነት ከወዝአደሩ ጋር መሰለፍ እን ዳለበት አይተናል ። እንግዲህ ዛሬ ወዝአደር ገበሬ ኅብረት መመሥረቱ አስፈላጊ የሚሆነውም የገ በሬው በሥልጣን መሳተፍ የሚገለጽበት ፤ የወዝ አደሩና የገበሬው ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት የሚከሰትበት መድረክ በመሆኑ ነው ። በዚህ አብ ዮት ገበሬው ከወዝአደሩ ጎን ይሰለፋል ካልን ፤ ወዝአደሩ ፓርቲውን መሥርቶ የገበሬውንና የወዝ አደሩን የአንድነት ግንባር በማቋቋም ሥልጣን ካል ያዘ በገበሬው ስም የመንግሥት ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም ። <u>ዛሬ የወዝአደር ፓርቲ ገና አልተቋ ቋመም ፤ ወዝአደር ገበሬ ኅብረት አልተመሠረተም ስለዚህ በገበሬው ስም የቀረበውም ጥያቄ በስሙ ለመነገድ ብቻ መሆኑ</u> ግልጽ ነው።

እንግዲህ ወዝአደሩና ገበሬው ድርጅቶቻቸ ውን መሥርተው ፤ በወዝአደር ገበሬ ኅብረት ሥር ያለ ሕዝባዊ ጦር አቋቁመው በኃይል ላይ የተመ ሠረተ ሥልጣን ካልያዙ በስተቀር ጥቂት ሰዎች መርጠው ስለላኩ ሥልጣን ያዙ ወይንም በሥ ልጣን ተካፈሉ ለማለት እንደማይቻል ግልጽ ነው ። ስለዚህ ወዝአደሩና ገበሬው የተጠቀሱት ለሽንገላና ለማጭበርበሪያ መሆኑ ነው ። እነዚህ ታላላቅ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከውስጡ ከወጡ ጊዜያዊ «ሕዝባዊ» መንግሥት የንዑስ ከበርቴና የቢሮ ከበርቴዎች መንግሥት ይሆናል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ሕዝባዊ ሊባል አይችልም ።

እስከ አሁን ስለጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥ ትና ስለጊዜያዊ «ሕዝባዊ» መንግሥት ካየነው የሚከተሉት ልዩነቶች ይገኛሉ ።

### ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት

፩. የዲሞክራሲ ጠላቶች ሳይደመሰሱ በሚደረግ ምርጫ ሰፊው ሕዝብ ሊጠቀም ይችላል ብሎ ያምናል ።
፪. ከልዩ ልዩ ክፍሎች በምርጫ ተውጣጥቶ የሚ ቋቋም መንግሥት ነው ።
፫. በምርጫ ከተቋቋመ በኋላ ተግባሩ የድርጅትና የትጥቅ ሥራ ማካሄድ ነው ።
፬. ሥልጣን ከያዘ በኋላ የሕዝብን ጠላቶች «ያወ ድማል »
፭. የንዑስ ከበርቴዎች መንግሥት ነው ።

### ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት

፩. የዲሞክራሲ ጠላቶች ሳይደመሰሱ በሚካሄድ ምርጫ ሰፊው ሕዝብ ምንም ጥቅም አያገኝም ብሎ ያምናል ።
፪. ከሕዝብ ተውጣጥቶ ሳይሆን በሕዝቡ አመፅ ላይ ተመርኩዞ የሚቋቋም መንግሥት ነው ።
፫. በነቃ ፤ በተደራጀና በታጠቀ የሕዝብ ኃይል ይመጣና ተግባሩ ነፃና የሕዝቡን ፍላጐት የሚገልጽ ምርጫ ማካሄድ ነው ።
፬. የሕዝብ ጠላቶችን ከደመሰሰ በኋላ ሥልጣን ይይዛል ።
፭. የወዝአደሩን የገበሬው ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት ነው ።

### ማ ጠ ቃ ለ ያ ፤

በሀገራችን ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካና የኢ ኮኖሚ ለውጥ በመካሄድ ላይ እንዳለ እናያለን ። አንድ የገበሬ ማኅበር ተወካይ እንዳሉት ለውጡ ከተራራ ላይ እንደሚወርድ ጎርፍ ነው ። ይህን ለውጥ የሚያግድ ኃይል ፍጹም የለም ። ይህን እንኳን ሰፊው ሕዝብ ዘውደኞቹ እነ አስፋ ወሰንም ሆኑ ኢምፔሪያሊስቶችን ቢሮክራቶች ተረድተውታል ። የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኅብረት የሚል ድርጅት ያቋቋሙት ዘውደኞቹ ስለዲሞክራሲ ፤ ስለመሬት ለአራሹ ሲያወሩ ይህን ሀቅ በመገንዘባቸው ነው ። ግን ሁሉም ለውጥ አንድ አይደለም ። ለኢምፔሪ

ያሊስቶች ፤ መሳፍንቶችና ቢሮክራቶች የሚጠቅም የጥገና ለውጥ አለ ። ለወዝአደሩና ለገበሬው የሚጠቅም አብዮታዊ ለውጥ አለ ። ዛሬ ስለአብዮቱ ገፍቶ ድል መምታት የሚጨነቁ አብዮታውያን ሁሉ የሚፈልጉት ለውጥ አብዮታዊ ለውጥ ነው። በሩሲያ አብዮት ሲካሄድ ሌኒን ሁለት ውጤቶች ታይተውት ነበር ወይ ። የአብዮት ኃይሎች ንቃታቸው ፤ ድርጅታቸውና ትጥቃቸው የተሟላ ሆኖ አብዮቱ በጠላቶቹ ላይ ወሳኝ ድል ያገኛል ። አለበለዚያ የአብዮቱ ኃይሎች ለዚህ ወሳኝ ድል በንቃት ፤ በድርጅትና በትጥቅ ብቁ ሳይሆኑ ይቀሩና የአብዮቱ ጠላቶች እርስ በርስ ተስማምተው አብዮቱን ያጨናግፉታል ። የ፲፱፻፭ የሩሲያ አብዮት እንደተጨናገፈና ለምን እንደተጨናገፈ እንዲሁም በአብዮታውያን መደቦች ላይ የደረሰውን ግድያና ጭፍጨፋ በቍጥር ፱ ጋዜጣችን ላይ ስላነሣነው እዚህ ላይ አንመለስበትም ።

የአብዮታችንስ ውጤት ? የአብዮቱ ኃይሎች እስከአሁን የተገኙትን ድሎች ለማስጠበቅና ወደፊትም ለመግፋት የንቃት ፤ የድርጅትና የትጥቅ ዝግጅታቸውን በቶሎ ካሟሉ በጠላቶቻቸው ላይ ወሳኝ ድል አግኝተው የወዝአደሩና የገበሬው ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዢነት ይመሠረታል ። አብዮቱም ከግብ ይደርሳል ። ይህ የአብዮቱ ኃይሎች ዝግጅት ለወሳኝ ድል ሳይበቃ ከቀረ ግን የአብዮቱ ጠላቶች የበላይነት ያገኛሉ ፤ ሰፊው ሕዝብ እስካሁን ያገኛቸውን ድሎች ይነጠቃል ፤ አብዮቱ ለጊዜውም ቢሆን ይቀለበሳል ። ፋሺዝም ይነግሳል ። አብዮታውያን በአድኃሪ ኃይሎች ይመታሉ ይህ እንዳይሆን ነው የአብዮት ደጋፊ የሆኑ ኃይሎች በሙሉ በቆራጥነትና በትጋት ትግሉን ማካሄድ፤በሰፊው ሕዝብ በኩል የንቃት ፤ የትጥቅና የድርጅት ድካሞች በቶሎ እንዲሟሉ መጣር ያለባቸው ።

የቦልሼቪኮችና የሜንሼቪኮች ልዩነት ያንዱ በሰፊው ሕዝብ ኃይል ላይ ቁርጠኛ እምነት መያዝ የሌላው ማወላወል ነበር ። ሌኒን እንዳለው ቦልሼቪኮች «ሕዝቡ ማለትም ወዝአደሩና ገበሬው የነፃነት ጠላት የሆኑትን ያለርኅራኄ እየደመሰሰ ፤ ጠላቶቹ የሚሰነዝሩትን የመልስ በትር በኃይል እያንኮታኮተ ፤ ለተረገመው የኢስያ አረመኔአዊነትና የሰው ልጅ መዋረድ ቅርስ ምንም ዓይነት አስተያየት ሳያደርግ ከዘውድ አገዛዝና ከመሳፍንት ጋር ያለውን ቁርሾ በተራው ሕዝብ መንገድ (ፕሌብያን ዌይ) እንዲወጣው ይፈልጋሉ ። »

በሀገራችንም ሀቀኛ አብዮታውያን በሙሉ የሚፈልጉት ይህንኑ ነው ። ጥረታቸው ወዝአደሩና ገበሬው ተደራጅተውና ታጥቀው ጠላቶቻቸውን በኃይል እንዲደመስሱ ወላዋይ በሆነው ንዑስ ከበርቴ ተወናብደው ትግላቸው እንዳይደናቀፍ ነው የሚታገሉት ። በሩሲያ ወዝአደሩ ወላዋይ ከሆነው ቡርዥዋው ጋር በሚያደርገው ትግል ( በሀገራችን ከቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴው) እጁ እንዳይታሰር ፤ መሪነቱን እንዳይነጠቅ የሚከተለውን ማድረግ እንደሚኖርበት ሌኒን ያስተምራል ።

«ባጭሩ ወላዋይ ከሆነው ቡርዧ ዲሞክራት ጋር በሚያደርገው ትግል እጁ እንዳይታሰር ወዝአደሩ ገበሬውን ወደ አብዮታዊ ንቃተ ሕሊና ከፍ ለማድረግ ፤ የማጥቃቱን ተግባር ለመምራትና ብሎም ቁርጠኛ የወዝአደሩን የዲሞክራሲያዊነት መሥመር በነፃ ለመከተል ተፈላጊውን ያህል የመደብ ንቃተ ሕሊናና ጥንካሬ እንዲኖረው ይገባል ።

—ወዝአደሩ ብቻ ነው ለዲሞክራሲ ቁርጠኛ ተዋጊ ሊሆን የሚችለው ለዲሞክራሲ በሚያደርገውም ትግል ድል አድራጊ የሚሆነው ሰፊው ገበሬ በአብዮታዊው ትግል ሲሳተፍ ብቻ ነው ። ወዝአደሩ ይህን ለማድረግ አቅም ካጣ ቡርዥዋው (በሀገራችን ንዑስ ከበርቴው) የዲሞክራሲያዊው አብዮት ግንባር ቀደም ይሆንና ወላዋይና ስግብግብ ባሕርይውን ለአብዮቱ ያጋራዋል ፤ ያጋባበታል ይህን ሁኔታ ሊያስወግድ የሚችለው የወዝአደሩና የገበሬው አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት ብቻ ነው ። » (ገጽ ፶፯—፶፰ ስርዝ የተጨመረ )

በሩሲያ ውስጥ ወዝአደሩ ጥንካሬ አግኝቶ ለዚህ ተግባር ብቁ እንዳይሆን ግራ ስለሚያጋቡት ስለሜንሼቢኮች ሲገልጽ ደግሞ እንዲህ ብሏል ።

«ስለ ድርጅት ልልነት እየሰበኩ ፤ . . . የአብዮታዊውን ወዝአደር የፖለቲካ መፈክሮች ከዘውደኛ ቡርዧዋው መፈክር ጋር እያምታቱ ፤»አብዮቱ በንጉሥ አገዛዝ ላይ ወሳኝ ድል« እንዳያገኝ እያወናበዱ ናቸው ። —ይህ ሁሉ ባንድ ላይ ሲወሰድ አብዮታዊ ሁናቴ ባለበት ጊዜ ጭራ የመሆንን መመሪያ ይመሠረታል ። ይህም ወደ ድል የሚወስደውን ብቸኛ ጎዳና ከማመልከትና የሕዝቡን አብዮታዊና ሪፑብሊካዊ ክፍሎች በወዝ አደሩ መፈክር አካባቢ በማሰለፍ ፈንታ ወዝአደሩን ግራ ያጋባዋል ፤ ይበታትነዋል ። ስለሆኔታው ያለውን ግንዛቤ ውዥንብር ውስጥ ይከተዋል የሶሻልዲሞክራሲን ታክቲኮችም ያቃልላል። » ገጽ/፶፰

እኛም መዋጋት ያለብን የድርጅት ልልነት የሚሰብኩትን ፤ የወዝ አደሩን አብዮታዊ መፈክሮች ከፊውዳሉና ከኢምፔሪያሊስት መፈክሮች ጋር የሚያምታቱትን ፤ በሕዝብ ጠላቶች ላይ ወሳኝ ድል የሚገኘው በነቃ ፤ በተደራጀና በታጠቀ የሕዝብ ትግል መሆኑን ሊያድበሰብሱ የሚፈልጉትን ሁሉ ነው። ይህን አለማድረግ ወዝ አደሩ ስለሁኔታው ተረድቶ ለታሪካዊ ተግባሩ ብቁ እንዲሆን ማድረግ ውዥንብር ውስጥ መክተቱ፤ ኃይሉም ከመሰብሰብ ፈንታ እንዲበታተን ማድረግ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ። ስለሆነም ተራማጆች ይህን መዋጋት ትተው፤ ወይንም በበቂ ሳይታገሉና ሳያጋልጡ ቀርተው ሰፊው ሕዝብ አሳሳች በሆኑ መፈክሮችና የትግል ዘዴዎች ባልሆነ አቅጣጫ እንዲባክን ተደርጎ ትግሉ ቢቀለበስ የኢትዮጵያ ተራማጆች ከታሪክና ከመጪው ትውልድ ወቀሳ አይድኑም።

ይ ቀ ጥ ላ ል።

## ጥ ያ ቄ

፩. በ፲፱፻፭ የሩሲያ አብዮት ጊዜ ሕዝባዊ ሸንጎ ለመጥራት ከተለያዩ ክፍሎች የቀረቡትን የተለያዩ ሀሳቦች አሳይ ።

፪. ሥልጣን ያለው ሕዝባዊ ሸንጎ ለመጥራት በቅድሚያ መኖሩ አስፈላጊ የሚሆነው ቁስ አካላዊ ሁኔታ ምንድን ነው ?

፫. በቦልሼቪኮችና በሜንሼቪኮች መሀከል ስለጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት አመጣጥ የነበረውን ልዩነት አሳይ ።

፬. በጊዜያዊ «ሕዝባዊ» መንግሥትና በጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት መሀከል ያሉትን ልዩነቶች አሳይ ።

፭. በሩሲያ ሜንሼቪኮችን ከዘውደኛ ቡርዧዋው ጋር ፤ በሀገራችን ቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴውን ከነመንገሻ ሥዩም ጋር ያሰለፏቸውን መፈክሮች እያነሣህ አድኃሪነታቸውን አሳይ። ዛሬ በሀገራችን አድኃሪ ኃይሎችን ነጥሎ ለብቻ የሚያሰልፍ ትግሉንም የሚያራምድ መፈክር ምንድን ነው?

፮. የድሮው ቡርዧ አብዮት በ፲፱፻፭ የሩሲያ አብዮት ላይ ያሳየውን ለውጥና ይህ ለውጥ ገፍቶ ሄዶ አዲሱ ቡርዧ አብዮት እስከመባል የደረሰበትን ምክንያቶች አስረዳ።የአብዮታችንን ይዘት ለመረዳት ጠቃሚ ስለሆን በዚህ ርእስ ላይ የተጻፉትን ልዩ ልዩ ጽሑፎች ፈልገህ አንብብ ። ለምሳሌ ፤ ስለአዲሱ ዲሞክራሲ ማኦ ሴቱንግ ፤ በታዬ በቀለ የተተረጎመ ፤ስለ ዲሞክራሲ ፤ የውይይት መነሻ ከሕዝብ ድርጅት የፍልስፍና ማስፋፊያ የተዘጋጀ ፤ አዲስ ፋና ቍጥር ፪ እና ፫ ፤አዲስ ዘመን ከጳጉሜ ፬ ጀምሮ በተከታታይ «አዲሱ ቡርዧ ዲሞክራቲክ አብዮትና ...»በሚል ርእስ የተጻፈ ።

# ለነቃ ለተደራጀና ለታጠቀ የሕዝብ ትግል